የሰው ዉስጡና ዉጪው ..

"ማሻእላህ ጠንካራ ነህ" አልኩት::

"እንዴት አወቅክ" አለኝ::

"ላይህ ላይ በማየው ነገር ነዋ፤ ዉስጥህን እንዴት ላውቅ እችላለሁ" አልኩት::

አትሳሳት አለኝ:: ከላይ በምታየው ነገር ብቻማ አትመን:: የተዘጋ ሳጥን ዉስጥ ምን እንዳለ አይታወቅም፤ መጽሐፍ ሽፋኑ ስላማረ ቆንጆ ነው አይባልም:: ቀጠለ-

ብዙ ሰው ጠንካራ እንደሆንኩ ያስበኛል:: ግን አይደለም:: ጠንካራ የሚመስሉ ላለመውደቅ ብየ በየቀኑ ስለምታገል ነው:: በዉስጤ ብዙ ስሜቶች አሉ፤ ብዙ መግቶች፣ ብዙ መጥፎ ጥሪዎችም አሉ:: አንዳንዴ ያሸንፉኛል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ አሸንፋቸዋለሁ:: አንዴ ከበላያቸው እሆናለሁ ሌላ ጊዜ ደግሞ አወድቃለሁ::

አትሳሳት አለኝ:: ሁላችንም ለአሉታዊ እጅ ላለመስጠት ነው የምንታገለው:: አንዳንሰበር ነው ቀና የምንለው:: ለራሣችን ስንል ቀና እንላለን:: ሰዎችን እኛን እይተው ቀና እንዲሉ ብለን ቀና እንላለን:: .... ለሚወዱኝ ስል ቀና እላለሁ፤ ለቤቴ ስል ቀና እላለሁ፤ ለእናት አባቴ ስል ቀና እላለሁ፤ ለልጆቼ ስል ቀና እላለሁ፤ ለምቀኛዬ ስል ቀና እላለሁ:: ቀና ለማለት ዉሜ ምን አማራጭ ስለሌለኝ ቀና እላለሁ:: ዉስጤን ብታይ እኮ ይሸን ሁሉ ጉድ ተሸክመህ ነው እንዴ የምትንቀሳቀሰው ልትለኝ ሁሉ ትችላለህ::

እና ወዳጄ አትሳሳት - የዱንያ እሣት ሁሉም ቤት ገብቷል፤ ፈተናዋ በየመስኩ ተጥዷል: : ነዉንዳንዱ ሳቅ ጀርባ ከባድ ልቅሶ አለ፤ ጤና ከሚመስል ፊት ኃላም ከፍተኛ ህመም ሊኖር ይችላል:: ድሉት ዉስጥ ናቸው ብለን የምንቀናባቸው አንዳንድ የሰዎች ፀጋዎች ሰዎቹ እየተጠቀሙበት ሳይሆን እየተቀጡበት ይሆናል ማን ያውቃል:: ሁሉት እየመረረው የሚኖር ስንት አለ:: ደስተኛ ነው የምንለው ሰው ፈገግታ ሽፋኑ ብቻ ቢሆንስ:: ተመችቶታል የምንለው ሰው የስቃይ ኑሮ እየኖረ ካለስ ምን አሳወቀን::

ብዙ ሰው እኛ የማናውቀው ብዙ ነገር አዉስጡ ይካሄዳል፤ በዉስጡም ብዙ ነገር ይኖራል:: ዱንያ ለማንም ፍዉም ሆና አታውቅም:: አህ ብለህ ብታዳምጠው ሁሉም የሚተነፍሰው አይጠፋዉም:: ትንሽ አንኳን ጆሮ ብትሠጠው የምትሰማው ዘግንኖህ ጥለኸው ትሮጣለህ::

ኢየረፍን

ከሐራም ወደኋላ ለንድ እርምጃ ወደኋላ ብትሸሽ ሐላል በሩጫ ወዳንተ ይመጣል።።

****

ዱንያ ላይ ስትኖር ... ካንተ በታች ሪዝቅ ያለጢን ሰው ተመልከት ትረጋጋለህ፤

ካንተ በላይ ጢባዳ ወዳለው ሰው ተመልከት ትበረታለህ።።

ግራ ቀኝ እይና ራስህን ዝምግም ያለህበትን ደረጃ ታውቃለህ።።

ወዳጄ! የጀነት ገበያ ጢድድሩ ለሁሉም ነው ከፍት የተደረገው።። ጠንከር ካሉት ጋር ተወዳደር።። ትከከለኛው ጢድድር የበለጠህን ሰው መወዳደር ነው።። ከደካማ ሰው ጋር መወዳደር ጢድድር አይባልም።። ለዚህም ነው በተለይ ከጢባዳ አንባር ዐይንህን ሶሐቦችና ታቢዒዮች ላይ ማድረግ ያለብህ።። ዲንህን ከፍ አድርገህ ያዝ።። ጠንካሮችን ማጣቀሻህና ጢላማህ አድርግ።። እነርሱን ባትቀድማቸው እንኳን ትከሻ ለትከሻ ተጋፋ።። ከአካለ ስንኩል ጋር ተወዳድረህ ኢማን አለኝ ጠንካራ ነኝ አትበል።። ቆይተው ከመጡ ደጋግ የአላህ ባሮች መካከል ቀደምቶቹ ደጋግ የአላህ ባሮች ጀነትን ብቻቸዉን እንዲወርሱ አንተዋቸዉም በጅ ላይ እንጋፋቸዋለን ይሉ ነበር።።

አይታመንም

- ዲን የሌለው ሰው አይታመንም፤
- አላህን የማይፈራ ሰው አይታመንም፤
- ታማኝ የልሆነ ሰው አይታመንም፤
- አስመሳይ ሰው አይታመንም፤
- ጢሸታም ሰው አይታመንም፤
- ሚስጢር የሚያባክን ሰው አይታመንም፤
- ቁሳዊ ሰው አይታመንም፤
- የጥቅም ሰው አይታመንም፤
- ራስ ወዳድ ሰው አይታመንም፤
- ጢላታ ካጅ ሰው አይታመንም፤
- በትርፍ ጊዜው የሚፈልግህ ሰው አይታመንም፤

የማይታመኑትን ተጠንቀቅ፤ ከማይታመኑት ላለመሆንም ተጠንቀቅ።።

የልቦና ንፅሕና

ስጦታ ለመግዛት ብሎ ባል ከሚሰራ ጋር ወደ ገበያ ሄደ። "ለእናቴ ሰጦታ ልግዛ አስቢያለሁና አስቲ አንች ምረጭ።" አላት። ሚስት ቅናት ቢሰኪ ተሰማት። ዋጋው ረከስ ያለዉን መረጠች። ባልም ዋጋዉን ከፈለና ሰጦታዉን አስጠቅልሎ ወደያሉት ተመለሱ። ማታ ላይ ባል ስጦታዉን እወጣና ለሚስቱ ሠጣት። "ሰጦታሽን በራሰሽ እጅ እንድትገገር ፈልጌ ነው።" አላት።

ይህ ከቅናት ጉዳቶች መካከል ትንሹ ማሳያው ነው። ልቦና ንፁህ ሳሆን ሲቀር ጉዳቱ በራስ ላይ ነው። ልብን ንፁህ ማድረግ ጉልበት የማይጠይቅ፣ ልፋትን የማይፈልግ ዒባዳ ነው። ግና ባለቤቱን ለጀነት ያበቃል። ያን ነቢዩ ሶ.ዐ.ወ. የጀነት ነው ያሉትን ሰዉዬ አስታውሱ። ወደ መኝታዬ ስሄድ በቀልቤ ዉስጥ ለአንድም ሙስሊም ቅሬታ ይዠ አልሄድም ነበር ያለው። በርግጥም ይህ ከባድ የልቦና ዒባዳ መሆኑ አይካደም። በአንድም ሰው ሳይቀኑና ሳይመቀኙ፣ ቅር ሳይሠኙ ወደመኝታ መሄድ ትልቅ ትግልን ይጠይቃል።

ምቀኝነት ትልቅ በሽታ ነው። ባለቤቱን በልቶ የሚጨርስ ደዌ ነው። አሳት እንጨት አንደምትበላው የአንድን ሰው መልካም ሥራ ይበላል። ምቀኝነት በሰማይ ቤት አላህ የታመፀበት የመጀመርያው ወንጀል ነው። ኢብሊስ በአባታችን አደም ቀና፤ ተመቀኘ። በአላህ የታዘዘዉን አልፈጽም አለ። በዚህም የተነሳ ከአላህ እዝነት ተባረረ።

ምድር ላይም የመጀመርያው ኃጢአት ምቀኝነት ነው ይባላል። ሃቢል አላህ ዘንድ ተቀባይነትን በማግኘቱ ምክንያት ወንድሙ ቃቢል ቀናበት። በመጨረሻም ወንድሙን አስከመግደል ደረሠ።

የልቦናን ንፁሕ መሆን አላህ ይወደዋል። ባለቤቱንም ይመነዳዋል። በአንድ ወቅት ነቢዩ ሶ.ዐ.ወ. ይመፀዉቱ ዘንድ ሰዎችን አነሳሱ። እያንዳንዱ ሶሐባ የአቅሙን ያህል ያለዉን መፀወቱ። ዑልበት ኢብኑ ዘይድ ግን ከማንዘብ ምንም የሚመፀዉቱት ያልነበረው የኑሣ ደሀ ነበር። "አላህ ሆይ ከዚህ የገለባ ፍራሽ እና ዉሃ ከምጠጣበት ባልዲ በስተቀር ምንም የለኝም። አላህ ሆይ እኔ ስሜንና ከብሬን መጽዉቻለሁ።" አለ። ነቢዩ ሶ.ዐ.ወ. ተሣቢ እንዲጣራ አደረጉ። "ማነው ሥሙንና ከብሩን የመፀወቱው የታለ?" አሉ። ዑልበት ኢብኑ ዘይድ ቀረበ። የአላህ መልዕክተኛም ሶ.ዐ.ወ. አላህ ምጽዋትህን ተቀብሎሃል።" አሉት።

ለነቢዩ ኢብራሂም ዐ.ሰ. ንግሥናን የሠጠው አላህ ነው!!

ሁላት ጓደኛሞችን አውቃለሁ:: አንደኛዋ ለጓደኛዋ መልካሙን ሁሉ የምታስብ ናት:: ለግንኙነታቸው ይበልጥ መጠናከር ትጨነቃለች:: ለደስታዋ ትደሰትላታለች፣ ሲሐዘኗም አብራ ትከፋለች፣ በየኢጋጣሚው እየጠበቀች ምን ልታደርግላት እንደምትችል ትጨነቃለች:: ስጦታ፣ ዚያራ፣ ስልክ ... ሀሳቧ ስለሷ እያርፍም:: አላህ ኑሮዋን ካሰፋላት ወዲህ ደግሞ ይህን ድርጊቷን አጠናክራ ይዛለች:: አላህ የሠጣት ወዳጇ ናትና:: አሷም አላህ የሠጠኝ ጓደኛዬ ናት ብላ ለዚህ ለዚያም ታወራለች::

ጓደኛዋ ግን በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቀዝቀዝ ብላባታለች:: የሷ ኑሮ ዝቅ ሲል የጓደኛዋ ከፍ በማለቱ ይሆን ብዬ ዳር ሆኜ አታዘባለሁ እኔ:: ኑሮዋ ተቀይሯል፣ ቤቷ ሰፍቷል፣ ባሷ መልካም ሰው ነው፣ ልጆቿ የሚገራርሙ ጥሩዎች ናቸው:: የዚያችኛዋ ግን በተቃራኒው ነው:: አንዲህ ነው ብላ ባትናገርም በኑሮዋ፣ በልጆቿ፣ በባሷ ሁኔታ ሳታስበው ስትነጫነጭ አያታለሁ:: ጓደኛዋ የሆነ ነገር ባገኘች ቁጥር ሮጣ ትነግራታለች:: ጓደኛዋ ግን በመደሠት ፋንታ ትደነግጣለች፣ በማይደበቅ መልኩ ቅናት ፊቷ ላይ ይነበባል:: መልካም አሳቢዋ ከዚህች ጓደኛዋ ጋር አንዴት መኖር አንዳለባት ግራ አንደተጋባች ስለጓደኛዋ መለዋወጥ ነገረችኝ:: አብሯት መኖሩም፣ መቁረጡም ከበዳት፣ መለየቱም አስፈራት::

የሆነ ቀን መግሪብ ላይ ኢማሙ ያነበበው የቁርአን አንቀጽ ነው ይህን ጉዳይ ይበልጡኑ ያስታወሰኝ:: የአንቀፁ ሀሳብ "አላህ ለሰዎች በሠጠው ችሮታ ስለምን ይመቀኛሉ!" የሚል ነው:: ቀጥሎም "ለኢብራሂም ቤተሰብ መጽሐፍን፣ ጥበብንና አንዲሁም ታላቅ ንግሥናንም ሠጠነው::" ይላል አንቀፁ:: (አን-ኒሳእ : 54)

እኔም ይህችን ደብዳቤ ሞነጫጨርኩላት:: ...

አህቴ ሆይ! ምን መሠለሽ:: የምድር ላይ ሕይወታችንን ታች እና ላይ፤ ትልቅ እና ትንሽ፣ ከፍ እና ዝቅ፣ ሰፊ እና ጠባብ፣ ድሃ እና ሀብታም አድርጎ የፈጠረው የፈጠረን ጌታ አላህ (ሱ.ወ.) ራሱ ነው:: አሱ ደግሞ በከፍፍሉ ፍፁም ፍትሃዊ ነው:: ተዋጠልን አልተዋጠልን የርሱን ከፍፍል ከመውደድ ዉጭ ምንም አማራጭ የለንም:: ደግሞም ምንም ማድረግ አንችልም:: ብንቆጣ፣ ብናኮርፍ፣ ብንፈርጥ ብንዘል ምንም አናመጣም::

በትንሣኤና ምጽዋትነት ነምኖንገኘው እርሱ የለም።አንደጢም ጢስባቸን ሞምር ያሳዳል። አላህም ይቆጣብናል። አላህ የወደደልንን በመውደድ ግን የአላህን ጢዴታ እናገኛለን። የልብ ከንቱነትንና መጥፎ ጭንንም እናተርፋለን።

ጡኗሮ! ለእ ይገባኛል ያልከዉን ነገር አላህ ለሌላው ቢሠጥ አትቅና። ንግድህ ቀንበቅህ የሌላው ቢኖቅ አትመቅኝ፤ ሌላው ተወዶ አንተ ብትጠላ አትናደድ። ጀሊሉ የሻዉን ይሠራል፤ የፈለገዉን ያደርጋል። ዐይንህ እያየ አንተ ታዛገቦና ሰጋጁ ወድቅህ ለመፀኖዉና መንጀለኛው ሊየልፍ ይችላል፤ ቀድሞ የተነሳው እያለ ኋላ ላይ የመጣው ከፊት ሊሆን ይችላል፤ ታናሽ እያለ ታላቅ ሊከብር ይችላል፣ መልከ ጥፉዋ አግብታ መልከመልካሚ ልትዘገይ ትችላለች። ይህን ሁሉ የሚሠራው አላህ ነው። አላህም ለሥራው ሁሉ ዓላማና ምክንያት አለው። እኛ ስለሥራዎቹ የምናውቀው ነገር ቢኖር ፍጡም በሆን መልኩ ፍትሃዊ መሆኑን ብቻ ነው።

ከኢስራኤላዊዮን ነገድ ብዙ ነቢያትን የላከው አላህ ነው፤ ለነቢዩ ኢብራሂም ዐሰ. ቤተሰብ በዓለም ላይ ብልጫን የሠጠው አላህ ነው፤ ለነቢዩ ሱለይማን ዐ.ሰ. ሥልጣንና ሀብትን የሠጠው አላህ ነው፤ ዩሱፍን በወንድሞቹ ላይ ያስበለጠው አላህ ነው፤ ሙሳና ሃሩንን ከአንድ ቤተሰብ ነቢይ አድርጎ የላከው አላህ ነው፤ ነቢዩ ሙሐመድን በነቢይነት ያላቀው አላህ ነው፤ መካን የምድር ላይ ቤቱ መገኛ ማዕከል ያደረገው አላህ ነው። አላህ ለሻው ሰው በሻው ጊዜ የሻዉን ይሠጣል። አላህ እንደሻው በሻው መልኩ የፈለገዉን ይመርጣል።

አህቴ/ ወንድሜ ... እንደ ሒስድና ቅናት ራስንም ሌላዉንም የሚጎዳ ነገር የለም። አላህ በሠጠው ነገር እንደመብቃቃት የሚያረጋጋ ነገርም የለም። ከዚህ አንፃር ማድረግ ያለብህ ልንገርህ። አላህ የአንድ አባትና እናት ልጅችን አንኳ ያበላልጣል። እሱ ሁሉ ነገር በእጁ ነዉና ለሚገባው ሰው የሚገባዉን ነገር ይሠጣል። ለሌላው በተሠጠው ነገር ተደሠት እንጂ አትቅና። ሌላው ሰው ባገኘው ችሮታ ዐይንህ አይቅላ አትቃጠል። ከሱ ሳይወሰድ ላንተም እንዲሠጥህ ጌታህን ለምን። ከርሱ ወሰደ ማለት ላንተ ሠጠ ማለት እንዳልሆነም አወቅ። አላህ ከሠጠ አዳልቷል አይባልም። ምቀኝነት ማለት አላህ ሲሳዩን በትከከል አላከፋፈለም አላደለም ማለት ነው። አላህ ከፉ ቅናትንና ሒስድን ከልባችን ያንሳልን።

አዋጅ አዋጅ ስሙኝማ! በአላህ እጅ ያለ ነገር በሰዎች ሕግ መሠረት አይከፋፈልም።

ዱንያ ዘዋሪ

ዩዱንያ ፋናት እንደጦርነት ቀናት ናቸው። አንዴ ታሸንፋለህ ሌላ ጊዜ ደግሞ ትሸነፋለህ። አንድ ቀን የበላይ ሌላ ቀን ደግሞ ከበታች ትሆናለህ። እንዳሸነፍክ ለትኖርም፣ እንደተሸነፍክም አትዘልቅም። ዱንያ ያንተ የሆነች ቀን ብለህ ሆነህ ተጠቀምካት። ባንተ የሆነች ቀን ደግሞ አምርረህ ታገሳት።

ዱንያ ብርቱ ታጋይ ናት። በርትትህ ፊትለፊቷ ካልቆምክ በመጀመርያው ምቷ ትዘርርሃለች። ጉትረህ ካልያዝካት አዳክማ ትጥልሃለች። ብዙዎች ይሆንኑ ባህሪዋን በፅኑ ሳይረዱ ያለብዙ ትግል ተዘርረዋል፤ በርካቶች ምቷ ደከሚቸው በበታኝ ተሸንፈዋል። ታግለው ታግለው ከፍ ባለ ሕይወት ላይ ያየናቸው ወርደው ተመልከተናቸዋል።

ዱንያ ዘዋሪ ናት። የትናንት ብርቱ ዛሬ ደካሞች ቢሆኑ አይገርምም፤ ወጣቶች የነበሩት ሲሸመግሉ፣ ለጋሽ የነበሩ ከሰው እጅ ሲወድቁ፣ ሲያከሙ የነበሩ ታካሚ ሲሆኑ፤ ባለሥልጣን የነበሩት ባለጉዳይ ሆነው እናያለን።

ቀናት መንግሥታት ናቸው። ይገላበጣሉ፤ ይገለበጣሉ። ቀናት የአላህ ሠራዊቶች ናቸው። ያነሳሉ ይጥላሉ። ይሄዳሉ ይመጣሉ። በዱንያ ቀናት መካከል አላህ ሱ.ወ. ብዙ ሥራዎችን ይሠራል። ከፈሉን ከፍ ሌላዉን ዝቅ ያደርጋል።

በምድር ላይ አስካለህ ድረስ ሁሉም ነገር ቅርብህ መሆኑን እወቅ። ግራም ቀኙም ቅርብ ነው። ከፍ ካልክ ዝቅታ ቅርብ ነው። ዝቅ ካልክም ከፍታህ ሩቅ አይደለም። ሀብታም ከሆንክ ድህነትን አትመን። ድሃ ከሆንክ ከሀብት ተስፋ አትቁረጥ። የታመምክ እንደሆን አልድንም ብለህ አትተከዝ። ጤነኛ ከሆንክ ሁሌም ብርቱ ነኝ ብለህ አትንጠባረር። ሐዘን ካገኘህ አያልፍም ብለህ አትቆዝም። ደስታ ላይ ከሆንክ ይዘወትራል ብለህ አትታለል። ወዳጄዋ! በአላህ እጅ ስላለው ነገር ምንም ዋስትና የለህም። የነገን አንተ አታውቅም። እንኳን የነገን የአሁኑ ምን ሚስጢር እንደያዘ አናውቅም። ነገን አትገምት። አውቀዋለሁ ብለህም አትዘናጋ። መልካም ነገር ብቻ ይዞ እንደሚመጣ ወዳጅ አድርገህ አታስበው። ነገ እንግዳ ነው ምን ይዞ እንደሚመጣ አይታወቅም። ሞት ይዞ ሊመጣ ይችላል፤ በሽታን አርግዞ ይሆናል፣ ድህነትን ተሸክሞ ይሆናል። ዱንያ አትረጋም። ፀባዩዋ ይቀያየራል። ዓለም ዘዋሪ ናትና ሁሌም መለዋወጧን ጠብቅ።